# <u>የስድስተኛ ክፍል አማርኛ የሞዴል ፈተና መለማመጃ</u>

## <u>ጥያቄ ሁለት</u>

### ምንባብ ፡ ቸር ጠባቂ

ጥያቄ፡ የጠባቂው ስራ ምንድን ነው ?

የሚበሉት ሳር ፤ የሚጠጡት ውሃ እንዲያገኙ የበጎቹን መንጋ መመልከት ነው ። ቀበሮ ወይም ተኩላና ነብር ይዟቸው እንዳይሄዱ መትጋት ነው። ጠባቂው ቀኑን ሙሉ ከበጎቹ ጋራ አብሯቸው ይውላል ፤ ሌሊትም በበረት ይዘጋባቸዋል፤ ፀሃይም በገረረ ጊዜ በጎቹን በሜዳ አይተዋቸዉም። ያለበለዚያ በሙቀ ይበተናሉ። ባውሬም ተበልተው ይቀራሉ። ብርቱ ዝናብ ቢጥልም አደጋ እንዳያገኛቸው አብሯቸው ሊሆን ይገባዋል።

በግ ሰውን የማይጎዳ እንስሳ ነው። መቃወምም አይችልም ፤ ከውሻ ፤ ቀበሮ ፤ ወይም ከነብር ራሱን ማዳን አይችልም ። በግ ሞኝ እንስሳ ነውና ከመንገድ የተሳሳተ እንደሆነ ፈልጎ ማግኘት አይቻልም ። የዱር አውሬ በሚጭቆት ይቀራል ፤ ወይም ጎርፍ ይወስደዋል ።

በጎቹን እና ጠቦቶቹን ከእሾህና ከጎርፍ ለማዳን አውሬውንም ለማባረር እጅግ ንቅ ሰው መሆን ለጠባቂው ይስፈልገዋል ። በጎችም አብዝተው እንዲመገቡ ጠቦቶቹንም በደከሙ ጊዜ እንዲሸከማቸውና ለምለም ሣር ወደ በቀለበት ፤ ጥሩ ውሃ ወዳለበት እንዲመራቸው ሩህሩህ መሆን ለጠባቂው ይገባዋል። ጠባቂው የጠፉትን በጎች ተከታትሎ ሄዶ ወደበረት እንዲመልሳቸው ታጋሽ መሆን ይገባዋል ፤ ስለበጎቹ የሚጠነቀቅ ነፍሱንም ስለርሳቸው የሚለውጥ እንዲሆን ይገባዋል።

ወንዶች ሴቶችና ልጆቻችንም እንደ በጎችና እንደ ግልገሎቻቸው ናቸው ። በቅን የሚመራቸው ፤ለከፉም የሚመከትላቸው እረኛ ግድ ያስፈልጋቸዋል ።

እንግዲህ ውደ ኃጢአት የሚወስደንና ከፉም እንድናደርግ የሚፈትን አንድ እባብ አለ ። ስለዚህ እንዲያስተምረንና ከኃጢያትም እንዲያድነን ወደ እግዚአብሔርም እንዲመልሰን አንድ ጠባቂ ያስፈልገናል ።

ቸር ጠባቂ ማነው ?

ከከበደ ሚካኤል  ከታሪከና ምሳሌ 2ኛ መጽሐፍ  የተወሰደ

LIVEWORKSHEETS

### ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልሱ

1. ከሚከተሉት ውስጥ የቸር ጠባቂ መገለጫ የሆነው የትኛው ነው ?

   ሀ) ታጋሽ  ለ) ሩህሩህ  ሐ) ንቅ  መ) ሁሉም

2. ነፍሱንም **__ስለርሳቸው__** የሚለውጥ ሲል የተሰመረበት ቃል ማንን ያመለክታል ?

   ሀ) ጠባቂዎቹን  ለ) እረኞቹን  ሐ) በጎቹን  መ) ሀ እና ለ

3. ተኩላና ነብር ይዟቸው እንዳይሄዱ **__ሙትጋት__** ነው። ሲል የተሰመረበት ቃል ፍቺ :

   ሀ) በጠበቅ  ለ) ታታሪ ጠባቂ  ሐ) የማይሰለች ጠባቂ  መ) ለ እና ሐ

4. የበጎቹን **__መንጋ__** መመልከት በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ምንን ያመለክታል:

   ሀ) አይነት  ለ) ብዛት  ሐ) መልክ  መ) ሁሉም

### ከዚህ በታች ለተቀመጡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የሆነውን ምረጡ

6. ............... በሕይወቴ ስንፍናን አልወድም :: በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ ሊያሟላ የሚችለው ተውላጠ ስም የቱ ነው ?

   ሀ) እነሱ  ለ) እኔ  ሐ) እሷ  መ) አንቺ

7. ከሚከተሉት መካከል ተውላጠ ስም የሆነው የቱ ነው ?

   ሀ) እሷ  ለ) አበባ  ሐ) ቅድስት

   መ) እሱ  ሠ) ሀ እና መ

8. ከሚከተሉት መካከል የክርክር አቀራረብ ምምሪያ የሆነው የቱ ነው ?

   ሀ) ራስን እና የመከራከሪያ ር ዕስን ለአድማጭ ማስተዋወቅ

   ለ) ፍሬ ሃሳቦችን በቅደም ተከተል ማቅረብ

   ሐ) ክርክሩን ረጋ ባለ መንፈስ ማቅረብ

   መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

9. አንድን ጉዳይ በበቂ ማስረጃዎችና መረጃዎችን የሚያብራራ የድርሰት አይነት .......... ነው ::

ሀ) ስዕላዊ ለ) አመዛዛኝ ሐ) ተራኪ መ) ገላጭ

10. ታላቅ ወንድሜ ዛሬ ከሆላንድ ይመጣል :: በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ ጊዜን የሚያመለክተው ተውሳከ ግሱ የቱ ነው ?

ሀ) ወንድሜ ለ) ዛሬ ሐ) ይመጣል መ) ሁሉም

11. ከሚከተሉት ዓ/ነገሮች ውስጥ ነጠላ ዓ/ነገር የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ጌም መጫወት እወዳለሁ ገን እንድጫወት አይፈቀድልኝም::

ለ) በባዓላት ጊዜ አዳዲስ ልብሶችን መልበስ እወዳለሁ::

ሐ) ህገወጥ ንግድ መነገድ ሀገርን እና ወገንን ይጎዳል::

መ) አስናቀች እና ዘሪቱ እህትማማቾች ናቸው::

12. ትናንትና ሲያሽከረክር የነበረው ሾፌር መንገዱን ስቶ **ማጥ** ውስጥ ገባ :: የተሰመረበት ቃል ፍቺ:

ሀ) ረግረግ ቦታ ለ) ቁልቁለት ሐ) ጉድጓድ መ) ሁሉም

13. የሰው ልጅ በስራው ደስተኛ............. ውጤታማ.............. እንደ ፍላጎቱ መሰማራት አለበት:: በባዶ ቦታው ላይ መግባት ያለበት አያይዥ ቃል:

ሀ) ነገር ገም/ስለዚህ ለ) እርግጥ ነው/ ቢሆንም

ሐ) እና/ ይሆን ዘንድ መ) መልሱ የለም

14. ..............እና.............. ተባብረው ቢሰሩ ኑሯቸውን ማሸነፍ ይችላል:: በባዶ ቦታው ላይ መግባት ያለበት ተውላጠ ስም:

ሀ) እነሱ እና እናንተ ለ) እኔ እና አንተ

ሐ) እሱ እና እሷ መ) እነሱ እና እኛ

LIVEWORKSHEETS

15. ከሚከተሉት ዓ/ነገሮች መካከል ነጠላ ዓ/ነገር የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ሀያትና መአዛ ትረካ ይወዳሉ

ለ) አለሙ ለእናቱ ውሃ ቀዳ

ሐ) ኳስ መጫወት እወዳለሁ ነገር ግን እንድጫወት አይፈወድልኝም

መ) ሀ እና ለ መልስ ናቸው

16. ከሚከተሉት ዐ/ነገሮች መካከል ውስብስብ ዐረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ናትናኤል ያነበበውን መፅሃፍ ለወንድሙ መለሰ

ለ) ያች ልጅ ጎበዝ ተማሪ ናት ነገር ግን መቅረት ታበዛለች

ሐ) ከትምህርት ቤት ሲመለስ የደንብ ልብሱን ቀየረ

መ) ሁሉም መልስ ናቸው

17. ከሚከተሉት ግሶች መካከል ኢ-ሳቢ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ጨለመ

ለ) አዘነ

ሐ) ሆነ

መ) ሁሉም

18. ከሚከተሉት ውስጥ የክርክር አተገባበር መርሆች ውስጥ የሚካተተው የቱ ነው ?

ሀ) ግልፅነት ያልተለየው አቀራረብ

ለ) በመረጃ ላይ የተመሰረተ አቀራረብ

ሐ) ስሜታዊነትን ማስወገድ

መ) የመከራከሪያ ርዕሰ ጉዳይ መምረጥ

ሠ) ሁሉም

19. ከሚከተሉት ዓ/ነገሮች መካከል በሃቅ ላይ የተመሰረተው የቱ ነው ?

ሀ) ሀፃናት በስነ-ምግባር ታንፀው ማደግ አለባቸው

ለ) ሁሉም ቋንቋዎች እኩል ናቸው

ሐ) ዘመናችን ሳይንስና ቴክኖሎጂ እየተስፋፋ የመጣበት ዘመን ነው

መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

20. ከሚከተሉት ውስጥ ልዩ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ዋና ቃል ለ) ነፃ ም ዕላድ ሐ) ጥገኛ ምዕላድ መ ) ትርጉም ያለው

21. **ፅጌረዳ** ለሚለው ቃል ፍካሬያዊ ፍቺ የሚሆነው:

ሀ) አበባ ለ) ፈጣን ሐ) ውብ መ) መስከረም

22. ውሻው ስለበረደው ............... ብሎ ተኝቷል፡፡

ሀ) ጥርግርግ ለ) ጥቅልል ሐ) ዘመም መ) ሀ እና ሐ

23. በፍቺ ልዩ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) አከናወነ ለ) ፈፀመ ሐ) ሰራ መ) ተወ

24. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል ነጠላ አረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ሃያትና መአዛ ትረካ ይወዳሉ።

ለ) አለሙ ለእናቱ ውሃ ቀዳ

ሐ) ኳስ መጫወት እወዳለሁ ነገር ግን እንድጫወት አይፈቀድልኝም

መ) ሀ እና ለ መልስ ናቸው

25. **"በፈግግታ ተሞልቶ"** ሲል.............. ማለቱ ነው፡፡

ሀ) ደስ ብሎት ለ) እየተዝናና

ሐ) እየሳቀ መ) ሀ እና ሐ

26. **"ውጤታማ"** የሚለው ቃል ................ ሊተካ ይችላል፡፡

ሀ) ደካማ ለ) አልሚ ሐ) ታታሪ መ) ስኬታማ

27. **"መቀበል"** ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆነው :

ሀ) መውሰድ ለ) መቅለብ ሐ) ማመን ሠ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

28. **<u>"ተሳለብኝ"</u>** ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆነው :

ሀ) ተዶለብኝ　　　　ለ) ታመነብኝ

ሐ) በአዕምሮዬ ተቀረፀብኝ　　　　መ) ስሉቴ ደረሰ

29. **<u>"ደሙ ፈላ"</u>** ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ትክክለኛ ፍቺ:

ሀ) ተናደደ　　　　ለ) በጣም ተቆጣ　　　　ሐ) ተደሰተ　　　　መ) ሀ እና ለ

30. አበበ ዛሬ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ **<u>ጆ ሮ ሰጠኝ</u>**:: የተሰመረበት ፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺ ምንድን ነዉ?

ሀ) አደመጠኝ　　　　ለ) አልሰማም አለኝ

ሐ) መያዣ አቀበለኝ　　　　መ) ሁሉም

31. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ሲጠብቅ እና ሲላላ ፍቺ የሌለው የቱ ነው ?

ሀ) ወተት　　　　ለ) አያት　　　　ሐ) መዳር　　　　መ) ነገር

ዘበርጋ አራት አመታት ያህል በዋሻና በጫካ ውስጥ ሲኖር ሹሩባው በወገቡ ከታጠቀው የቆዳ ዝናር በታች ወርዶ ይታይ ነበር በጎታ ገበያም ሆነ በሌሎች ስፍራዎች አጋጣሚት ያየችው ሴት ሁሉ **2** አይኔ ይፍሰስልህ ሳትል አታልፍም ነበር ሴቶች ሁሉ እሱን ለማየት **3** ለማግባት ይመኙት ነበር::

32. በተራ ቁጥር 1 ላይ መግባት ያለበት ስርዓተ ነጥብ የቱ ነው?

ሀ) ፣　　　　ለ) ::　　　　ሐ) ፤　　　　መ) :

33. በተራ ቁጥር 2 ላይ መግባት ያለበት ስርዓተ ነጥብ የቱ ነው?

ሀ) ፣　　　　ለ) ፤　　　　ሐ) ‹‹　　››　　　　መ) ::

34. በተራ ቁጥር 3 ላይ መግባት ያለበት ስርዓተ ነጥብ የቱ ነው?

ሀ) ::　　　　ለ) ፣　　　　ሐ) ‹　　›　　　　ሀመ) መ/የለም

35. ከሚከተሉት ውስጥ የመስሪያቤት ደብዳቤ ማካተት ያለበት የቱን ነው ?

ሀ) ቁጥር፣ ቀን　　　　ለ) ማህተም

ሐ) የመደበኛ ቋንቋ አጠቃቀም　　　　መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

36. <u>**ማጀት**</u> ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ጓዳ　　　　ለ) ማዕድ ቤት

ሐ) አደባባይ　　　　መ) ሀ እና ለ

37. ከሚከተሉት ውስጥ ማሾፍን፣ ማሽሟጠጥን ለመግለጽ የሚያገለግል ስርዓተ ነጥብ የቱ ነው?

ሀ) ::　　　　ለ) !　　　　ሐ) ፤　　　　መ) :

38. ህፃኑ ልጅ <u>**የብር ፍልቃቂ**</u> ይመስላል:: የተሰመረበት ቃል ፍቺ

ሀ) በጣም የሚያምር　　　　ለ) አስቀያሚ

ሐ) በጣም ሳቂታ　　　　መ) ነጭ የሆነ

39. መራኸ ትኳሹን እኛ ስናውቀው፣

ዝናር በአቅፌ ምን አስጨነቀው ::

ይሄ ግጥም በምን ሰዓት የሚገጠም ነው?

ሀ) በሃዘን　　　　ለ) በፉከራ　　　　ሐ) በልመና　　　　መ) በሙሾ

40. ዝናር በአቅፌ ሲል ምንን ይገልፃል

ሀ) ጉብዝናን　　　　ለ) ፍርሃትን　　　　ሐ) ሀይለኝነትን　　　　መ) ኩራትን

LIVEWORKSHEETS